# እንኳን ደህና መጡ

ለኤሌክትሮሳይኮሎጂ *(electrophysiology (EP))* ሂደት በ Inova Heart and Vascular Institute (IHVI) ለማካሄድ ቀጠሮ ይዘዋል፡፡ እባክዎትን በባለሙያና በሚንከባከብ እጅ ውስጥ መሆኖን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ በ IHVI፣ ሃኪሞቻችን፣ ነርሶቻችና የልብ ህክምና ባለሙያዎቻችን በሂደቶና ከኛ ጋር በሚኖሮት ቆይታ እጅግ ጥሩ የሆነ እንክብካቤ ለእርስ ለማድረግ ዝግጁ ናቸው፡፡ ጥያቄ ካሎት እባክዎትን ለሀኪም፣ ነርስ ወይ የልብ ካቴተርዚት ላብራቶሪ (cath lab) ሰራተኞች ይጠይቁ፡፡

## ስለሂደቶ

EP ሂደት (EP ጥናት ተብሎ ይጠራል) የልቦን ኤሌትሪካል ስርአት ለመመርመርና የመድሃኒቱን ውጤትና የልብ ምቶን ይመረምራል፡፡ በዚህ ጥናት ወቅት በብሽሽቶ ወይ በአንገቶ አማካኝነት ልብዎ ላይ ጥቃቅን ኤሌክትሮዶች ይገባሉ፡፡ የልብ ኤሌክትሮድ የልብ ኤሌክትሪካል ምልክቶችን ይለካል፡፡

## ሂደቱ የሚካሄድበት መርሀግብር፡

ቀን፡ ______________________________
*(Date)*

ቦታ፡ ______________________________
*(Location)*

የሚገኙበት ሰዓት፡ ______________________________
*(Arrival Time)*

የሂደት ሰዓት፡* ______________________________
*(Procedure Time)*

** እባክዎትን በቀጠሮዎ ቀን ድንገተኛ አደጋ ካጋጠመ የሂደቱ መርሀግብር ሊቀይር ይችላል፡፡ ማንኛው ለውጥ ካለ እናሳውቆታለን፡፡*

INOVA®

# የሂደት ዝግጅት

## ሂደቱ ከመካሄዱ 14 ቀናት በፊት፡ የላብራቶሪ ስራዎች ማጠናቀቅ

ሆስፒታሉ ውጤቶ ግዜውን ጠብቆ እንዲደርሰው የላብራቶሪ ምርመራ ከሂደቱ 3 ወይ 14 ቀን በፊት መካሄድ ይኖርበታል፡፡ ኢንሹራንስ ሽፋን ያለውን ማንኛውም ላብራቶሪ መምረጥ ይችላሉ፡፡

**የላብራቶሪ ኣገልግሎት ቦታዎች**

የ Inova Laboratories በመላው ኖርዘርን ቨርጂንያ አካባቢ ለላብራቶሪ ስራና ምርመራ ቀጠሮ ይሰጣል፡፡ አድራሻና የስራ ሰዓት ለማወቅ **inova.org/locatelab** ይጎብኙ፡፡

**ሂደቱ በ Inova Fairfax Medical Campus ከተካሄደ**
የላብራቶሪና ምርመራዎን በግቢው ውስጥ በ Inova Pre-Procedural Evaluation Clinic ቀጠሮ መያዝ ይችላሉ፡

Pre-Procedural Evaluation Clinic
Inova Professional Services Building, Ground Floor
3300 Gallows Rd., Falls Church, VA 22042

የላብራቶሪ ስራ ሰዓት፡ ከሰኞ እስከ ዓርብ 7 ጥዋት እስከ 6:30 ከሰዓት
ስልክ፡ **703.776.2000**
ፋክስ፡ **571.472.6508**

## ከሂደቱ አንድ እስከ ሶስት ቀናት በፊት፡ ቃለ መጠይቅ ስልክ ጥሪ

ሂደቱ ከማካሄዱ በፊት በስልክ ቃለ መጠይቅ የሚደረግሎት ሲሆን ይህም መረጃ ለመሰብሰብ፣ የተለዩ ፍላጎቶችን ለመለየትና ተጨማሪ ማብራርያ ለመስጠት ነው፡፡ የስልክ ጥሪ ካልተደረገሎት ሂደቱ በሚካሄዲበት ቀን የሚከተሉትን መረጃዎች ይዘው ይምጡ፡

- አሁን የሚወስዱትን መድሃኒት መጠንን ሰዓትና ንዲሁም ትእዛዝና ያለትእዛዝ የሚወስዱትን መድሃኒት፣ ተጨማሪ ቫይታሚኖች
- አለርጂክ የሚሆንቦት መድሃኒት/ምግብ/ፕላስቲክ ይዘርዝሩ
- የከዚህ በፊት ቀዶ ጥገናና መድሃኒት ታሪክ ይዘርዝሩ
- ሌላ ማንኛውም አስፈላጊ የመድሃኒት መረጃ

***መሰረዝ፡ ሂደቱን መሰረዝ ከፈለጉ፣ በጣም ከታመሙ፣ ወይ የጤና ሁኔታ ለውጥ ካሎት መሆን አለበት፣ በተቻሎት ፍጥነት ወደ ሀኪሞ ይደውሉ፡፡***

# የቅድመ-ሂደት ቃለ መጠይቅ ረቀት

እባክዎትን ከነርስ ጋር ለሚነሮት የስልክ ቃለ መጠይቅ የሚከተሉትን መረጃዎች ዝግጁ ያድርጉ፡

**በአሁኑ ግዜ የሚወስዱት መድሃኒት ስም**
*(ከሀኪም ትእዛዝ ውጪና ተጨማሪ ንጥረነገሮች)*

| የመድሃኒት ስም | ያወሳሰድ መጠን | የወሰደው ሰዓት |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

**ከዚህ በፊት ያካሄዱትና ማደንዘዣ ያስፈለጋቸውን ሌሎች ሂደቶች**

| ሂደት | ማደንዘዣ | ቦታና/ቀን |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

**ስፔሻሊስትና አንደኛ ደረጃ እንክብካቤ ሀኪሞን ይግለፁ**
*እባክዎትን ያስታውሱ፡ ካርድዮሎጂ፣ ፑሎሞኖሎጂ፣ ሄማቶሎጂ/አንኮሎጂ፣ ኒሮሎጂና የህመም ማስታገስ ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ እንዲሁም የጤና ሁኔታዎን መሰረት በማድረግ ሌሎችም ሊያስፈልጉ ይችላሉ፡፡*

| የታዘዘው ምርመራ | የት | መቼ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

**የምግብና መጠጥ መመርያ**

- ከሂደቱ 24 ሰዓታት በፊት አያጭሱ ወይ አልኮልወይ ካፊን ያላቸው መጠጥ አይጠጡ፡፡
- ከሂደቱ በፊት ከለሌት ጀምረው ምግብ አይመገቡ፣ አይጠጡ ወይ ማስቲካ አያኝኩ፡፡

### መድሃኒቶች

- ሀኪሞ ሁል ግዜ የሚወስዱትን መድሃኒት ለጊዜየው ያስተካክላል፣ በተለይም ስኳር በሽተኛ ከሆኑ፡፡
- አንቲኮግናታል መድሃኒት መውሰድ የሚያቆሙት (ደም ማቅጠኛ) በ:

  ______________________________

- ግሉኮፎጅ (ሜታፎርሚን) መውሰድ የሚያቆሙት በ:

  ______________________________

- መድሃኒት የሚመለከቱ ሌሎች የተለዩ መመርያዎች:

  ______________________________

- ስኳር በሽተኞች: እባክዎትን የኢንሱሊን መድሃኒት መጠንና ስለ ሚዋጠው የስካር መድሃኒት በተመለከተ ከሀኪሞ ጋር ይነጋገሩ፡፡
- የተለመደውን መድሃኒቶን ወይ ማንኛውም ሌላ መድሃኒት መውሰድ ካለቦት ሀኪሞን ይጠይቁ፡፡ ከሆነ፣ በጥቂት ውሃ ለመውሰድ ጥረት ያድርጉ፡፡

### መጓጓዣ

እርስዎ ሂደቱን ካካሄዱ በኋላ መድሃኒቱ ጎንዮሽና የእንቅስቃሴ ገደብ ስለሚኖረው ከ24 እስከ 48 ሰዓት ባለው ውስጥ መኪና መንዳት ስለማይችሉ ከሆስፒታል ወደ እቤት የሚጓጓዙበትን መንገድ ከሀላፊነት ከሚሰማው አዋቂ ሰው (18 ወይ ከዛ በላይ) ጋር መጓዝ ይኖርቦታል፡፡

በግል መኪና ወይ ታክሲ መጓዝ ይችላሉ፡፡ ነገርግን ሀላፊነት የሚሰማው ሰው ከእርስዎ ጋር መኖር ይኖርበታል፡፡

### ቅድመ-ሂደት ቆዳ ማጠብ

በሀኪሞ ወይ ቅድመ ሂደት ሰራተኞች ከታዘዘ እባክዎትን በአካባቢዎ ከሚገኘው መድሃኒት ቤት Hibiclens ይግዙ፡፡ በመድሃኒት ቤት ይገኛል፡፡

Hibiclens በቀዶ ጥገና ወቅት ኢንፌክሽን ስጋት የሚቀንስ ክሎረክሲን ግሉተን አንትስፔቲክ ማፅጃ ነው፡፡

እባክዎትን ቆዳዎን ለማፅዳት መመርያውን ይከተሉ:

- <u>ሁለት</u> ግዜ ገላዎን ይታጠቡ፤ አንድ ከሂደቱ በፊት ማታና ጥዋት ወደ ሂደቱ ከመምጣቶ በፊት፡፡ ገላዎን መታጠብ አለቦት መታጠብያ ገንዳ ላይ ግን አይታጠቡ፡፡
- ሂደቱ ከመካሄዱ ቢያንስ 48 ሰዓት በፊት የሰውነት ፀጉሮን አይላጩ፡፡ የፊት ፂም መላጨት ይችላሉ ነገር ግን ገላዎን ከመታጠቦ በፊት ያድርጉት፡፡
- መጀመርያ ገላዎን ሲታጠቡ፣ ከሂደቱ በፊት ማታ ገላዎን ሲታጠቡ:
  - ፀጉሮ ላይ ሻምፖ አድርገው ይታጠቡ በመቀጠልም ገላዎን በተለመደው ሻምፖና ሰሳሙና ይታጠቡ፡፡
  - በመደበኛው ሻምፖና ሳሙና ገላዎን ከታጠቡ በኋላ በእጅዎ Hibiclens ያድርጉ፡፡ ከአንገቶ በታች በመጀመር በቀስታ ገላዎን ይሹት፡፡ **Hibiclens ወደ ፀጉሮ፣ ጭንቅላቶ፣ ፊቶ፣ ስስ ህዋስ ሽፋን ወይ ሀፍረተ ስጋዎ በቀጥታ እንዳያስነኩ፡፡**
  - በውሀ ከመታጠቦ በፊት ተቀብተው ሶስት ደቂቃ ይቆዩ፡፡
  - ማፅጃውን በውሃ ከታጠቡ በኋላ በንፁህ ፎጣ ሰውነቶን ያድርቁ፡፡
  - ንፁህ የሌሊት ልብስ ለብሰው ንፁህ አንሶላ ላይ ይተኙ፡፡ በዚህ ምሽት ማንኛውንም የቤት እንስሳ በመኝታ ቤቶ እንዳያስገቡ፡፡
- ሁለተኛ ግዜ ገላውን ሲታጠቡ፣ ሂደቱ በሚካሄድበት ጥዋት:
  - Hibiclens ከመጠቀሞ በፊት መደበኛ ሳሙና **እንዳይጠቀሙ፡፡**
  - በእጅዎ Hibiclens ከአንገቶ በታች በማድረግ ገላዎን ይሹት፡፡ **Hibiclens ወደ ፀጉሮ፣ ጭንቅላቶ፣ ፊቶ፣ ስስ ህዋስ ሽፋን ወይ ሀፍረተ ስጋዎ በቀጥታ እንዳያስነኩ፡፡**
  - በውሀ ከመታጠቦ በፊት ተቀብተው ሶስት ደቂቃ ይቆዩ፡፡ Hibiclens ከተጠቀሙ በኋላ በመደበኛ ሳሙና እንዳይታጠቡ፡፡
  - ማፅጃውን በውሃ ከታጠቡ በኋላ በንፁህ ፎጣ ሰውነቶን ያድርቁ፡፡
  - ሆስፒታል ሲመጡ ንፁህ ልብስ ይልበሱ፡፡
  - ቀዶ ጥገና በሚካሄድበት ቀን ማንኛውም ክሬም፣ ሎሽን፣ ፓውደር፣ ሽቶ ወይ ዴዶራንት አይጠቀሙ፡፡

## የሂደቱ ቀን

- የጥዋጥ መድሃኒቶን ለመውሰድ ጥቂት ውሃ ብቻ ይጠጡ፡፡
- ሂደቱ በሚካሄድበት ጥዋት ገላዎን ይታጠቡ፡፡
- ሎሽን ወይ ሽጦ አይቀቡ፡፡
- ጥርስዎን በቡሩሽ ማፅዳት ይችላሉ፣ ነገር ግን ሳሙናውን እንዳይውጡ፡፡
- ሁሉንም ጌጦች ያውልቁ (የተበሱትንብ ጨምሮ)፡፡
- ሁሉንም ጠቃሚ ብረቶን እቤትዎ ያስቀምጡ፡፡
- ምቹና ሰፋ ያሉ ልብሶችን ይልበሱ፡፡
- የሚከተሉት ይዘው ይምጡ:
  - ፎቶ ያለወ መታወቅያ/መንጃ ፈቃድ
  - ኢንሹራንስ ካርድ
  - የጋራ ክፍያ፣ አስፈላጊ ከሆነ
  - ለጤና እንክብካቤ ወይ ኑዛዜዎ ቀድሞ የሚሰጥ የህክምና መመርያ ቅጂ
  - ምርኩዝ፣ ዎከር፣ ከዘራ ወይ ሌሎች አጋዥ መሳርያዎች ያስፈልጋሉ
  - እቤት ውስጥ ኦክስጅን የሚጠቀሙ ከሆነ፣ ከቤት ወደ ሆስፒታልና ከሆስፒታል ወደ ቤት ለመጓዝ የሚበቃዎትን ይዘው ይምጡ
  - ለመነፀር፣ ኮንታክት ሌንስ፣ ለደንቸር፣ የማዳመጫ መሳርያዎች፣ ወዘተ ማስቀመጫ ያምጡ
  - CPAP ማሽን ከማስክ፣ ትቦና ማስቀመጫ፣ አስፈላጊ ከሆነ
  - ኢንሄለር፣ የሚጠቀሙ ከሆነ
  - ላአዳር የሚሆን የሽንትቤት መፀዳጃዎች
  - አሁን የሚጠቀሙትን መድሃኒት ምን ያህል ግዜ እንደሚወስዱና መጠኑን መዘርዘር

### እሚደርሱበት፣ የሚገቡበትና ዝግጅት

**ሂደቶ ቀጠሮ የተያዘው በ Inova Heart and Vascular Institute (IHVI) በ** Inova Fairfax Medical Campus **ከሆነ ሂደቱ ከመጀመሩ** ሁለት ሰዓት በፊት ነው። ነገር ግን፣ በሆስፒታሉ መቼ መምጣት እንዳለቦት ይነገሮታል።

የታካሚ/ጠያቂ በግረይ ጋራዥ ማቆምያ በ IHVI ትይዩ ወይ ከ IHVI አጠገብ በሚገኘው የ Inova Fairfax Hospital Surgical Center መግብያ ቫሌት አገልግሎት ይጠቀሙ። በ IHVI ህንፃ ምድር ቤት በመግባት ወደ Cath/EP እንግዳ መቀበያ ይግቡ።

**ሂደቶ ቀጠሮ በ Inova Alexandria Hospital ከሆነ ከቀጠሮዎ** አንድ ሰዓት አስቀድማቹህ ድረሱ ወይ ሀኪሞ እንዳዘዞት ያድርጉ።

**ሂደቶ ቀጠሮ በ Inova Loudoun Hospital ከሆነ ከቀጠሮዎ** 90 ደቂቃ አስቀድማቹህ ድረሱ ወይ ሀኪሞ እንዳዘዞት ያድርጉ። ለ8 ጥዋት የተቀጠሩ ታካሚ 7 ጥዋት መገኘት አለባቸው። ሲደርሱ በእንግዳ መቀበያ ወደ እሚገኘው መመዝገብያ ቦታ ይሂዱ።

***ለሆስፒታል አድራሻ፣ አቅጣጫና መኪና ማቆምያ መረጃ፣ ከጀርባ ይመልከቱ።***

እባክዎትን በቀጠሮዎ ቀን ድንገተኛ አደጋ ካጋጠመ የሂደቱ መርሀግብር ሊቀይር ይችላል። ሂደቶ የሚጀመርበትን ሰዓት ላይ ለውጥ የሚያየመጣ ነገር ካለ እናሳውቆታለን።

**አንዴ ከገቡ በኋላ:**

- ነርስዋ ወደ ቅደመ ሂደት አካባቢ እንድትወስዶት ይጠብቁ።
- ወደ ግል መልበሻ ይወሰዳሉ።
- ከሂደቱ በፊት ሽንቶን እንዲሸኑ ይጠየቃሉ።
- የሆስፒታል ልብስ እንዲቀይሩና ስኪድ ካልሲ እንዲቀይሩ ይጠየቃሉ።
- ሁሉንም አጋዥ መሳርያዎች (ክራንች፣ ምርኩዝ፣ ዊልቸር፣ ተንቀሳቀ,ቃሽ አክስጅን፣ ወዘተ) ከእርስዎ ጋር ከመጣው ሀላፊነት የሚሰማው አዋቂ አስቀምጠው ይገባሉ።
- ነርስዎን ቅበላዎን፣ ዋናዋና ምልክቶችና የህክምና ታሪኮን በማጠናቀቅ ሂደቱን ትገመግማለች።
- በጥናታዊ ሙከራ ከተመዘገቡ ወይ ብቁ ከሆኑ የክሊኒኩ ጥናታዊ ሙከራ አስተባባሪ ከእርስዎ ጋር ሊገናኝ ይችላል።
- ኢንተርቨስ *(intravenous (IV))* መስመር በቬኖ ውስጥ የሚተከል ሲሆን ይህም በሂደቱ ግዜ ፈሳሽና መድሃኒት እንዲወስዱ ነው።

## ቤተሰብ/ጓደኞች ማምጣት

### ከሂደቶ በፊት

የተወሰነ ቤተሰብ/ጓደኛ አብሮት ሊመጣ ይችላል። የቅበላ ስነስረአቱ ቀተጠናቀቀ በኋላ በቅድመ ሂደት ደረጃው ላይ ሊያገኞት ይችላሉ።

### በሂደቱ ወቅት

ጠያቂዎች ብእንግዳ መገበያ ወይ ሌሎች ሆስፒታሉ ቦታዎች ሊጠብቁ ይችላሉ። በማቆያ ክፍሉም መለያ ኤሌትሮኒክ ቦርድ ላይ ማየት የምትችሉት የተለየ ቅፅ ይሰጣቸዋል።

### ከሂደቱ በኋላ

ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቤተሰብና/ጓደኞች በማገገምያ ክፍል እንዲቀላቀሎት ይጋበዛሉ። ከሂደቱ በኋላ ሀኪሞ ከእርስዎና ከቤተሰቦች ጋር ይነጋገራሉ።

## በሂደቱ ወቅት

EP ሂደት ከአንድ እስከ አራት ሰዓታት ሊወስድ ይችላል። ሀኪሞና አንስቴሎጂስቶቹ አጭር የህክምና ታሪኮን ለማወቅና ያልዎትን ማንኛውም ጥያቄ ለመመለስ ከሂደቱ በፊት ያናግርዎታል።

ለእርስዎ እንክብካቤ የሚያደርጉት የቡድን አባላት ሀኪም፣ የተመዘገቡ ነርሶች፣ ካርድዮቫስኩላር ቴክኖሎጂስት፣ አንስትዮሎጂስት ወይ ነርስ አንስቲስት። በዚህ ሂደት ወቅት ቦታውን ንፅህና ለመጠበቅ የቡድኑ አባላት ማስክና ጋውን ይለብሳሉ።

EP ላብራቶሪ ከገቡ በኋላ በኦፐሬቲንግ ክፍሉ ይተኛሉ። ልዩ መቆጣጠርያ መሳርያውም በደረቶና ጀርባዎ ላይ ይደረጋል። እርስዎን ደህንነት ለመጠበቅና ምቾቶን ለመጠበቅ በእግርዎ፣ እጅዎና ክንድዎ ላይ ፎም ፓዲንግ ይደረጋል።

በሂደቱ ወቅት ምቾት እንዲሰማዎት የሚያስፈልጎትን መድሃኒት ሀኪሞ ይወስናል። ይህም ከሂደቱ በፊት ይነገሮታል።

በራጅና ኤሌክትሮካዲግራም መንበብያ ክፍሎች ላይ የተለየ ክትትል ይኖራል። ክፍሉም ቀዝቃዛይሆናል እንዲሁም የሚያሞቅ ብርድልብስ ይሰጦታል።

## በአፋጣኝ ከሂደቱ በኋላ

### EP ጥናትና እብጠት ያስወገደ ታካሚዎች

- ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ካቲተሩ ይወጣል፤ በመቀጠልም በተወጋው ክፍል ላይ ደም መፍሰስ እንዳይኖር 10-20 ደቂቃ ያህል ማንዋሊ መጫን።
- ደም መፍሰስ ካቆመ በኋላ ባንዴጅ ይደረጋል።
- አርተርያል ካቲተር ተተክሎ ከነበረ በተወጋው ቦታ ለይ ድረሲንግ ፕሬዠር ጥቅም ላይ ይውላል። ደም መፍሰስ ወይ መፈንዳት እንዳያጋጥም ሂደቱ ከተካሄደ በኋላ ለስድስት ሰዓት መተኛት አስፈላጊ ነው።

- ጭንቅላቶን ወደ ላይ አያንሱ ወይ ጉልበቶን አይጠፉ፡፡
- በቁስሉ ላይ ደም መፍሰስ ካጋጠመ ቦታው ላይ በመጫን ለአራት ሰዓት መተኛት ይኖርቦታል፡፡
- ከሂደቱ 24 ሰዓት በኋላ ባንዴጁን መላጥ ይችላሉ፡፡
- ከሂደቱ 24 ሰዓት በኋላ ገላዎን መታጠብ ይችላሉ ነገር ግን ባንዴጁን መልሰው እንዳይለጥፉ፡፡

## ICD/የልብ ምት መቆጣጠርያ የሚጠቀም ታከሚ

በሰውነቶ ላይ መሳርያ ከተተከለሎት፣ በተተከለው አካባቢ ያለውን እጅ ማንቀሳቀስ የለቦትም፡፡ ከደረቶ በላይ እንዲይዙትና ምንም ዓይነት ነገር እንዳያነሱ ለማስታወስ ማንጠልጠያ ይደረግሎታል፡፡

## ሁሉም ታካሚዎች

### እንቅስቃሴ

- ሁልግዜ መታወቅያዎን ይዘው ይንቀሳቀሱ፡፡
- ከሂደቱ በኋላ ብያንስ ለ24 ሰዓት መኪና አያሽከርክሩ፡፡
- በመጀመርያው ቀን እረፍት ያድርጉ፣ በሂደትም እንቅስቃሴ በመጨመር በቀጣይ ቀናት ወደ ነበረበት እንቅስቃሴ መመለስ፡፡
- እሚቻል ከሆነ ሂደቱ ከተካሄደ ለ24 ሰዓት ደረጃ አይጠቀሙ፡፡ ደረጃ መጠቀም ካለቦት ያልተጎዳውን እግሮን በማስቀደም አንድ በአንድ ይውጡ፡፡ በሽሽቶን ማግኘት ከቻሉ አጥብቀው ይያዙ፡፡
- ለቀጣዮቹ አምስት እስከ ሰባት ቀናት 10 ፓውንድ ወይ ከዛ በላይ ክብደት አያንሱ፡፡ ይህም መግፋት፣ መሳብ፣ መጎተት ወይ ማንቀሳቀስ ይጨምራል፡፡
- ለቀጣዮቹ አምስት ቀናት ሃይል የሚፈልጉ እንቅስቃሴዎችን አያድርጉ፡፡ ድካም፣ አየር እጥረት፣ ላብ ወይ ደረት ህመም የሚፈጥሩ ነገሮችን አይሞክሩ፡፡

### ቁስልና ቀዶ ጥገና እንክብካቤ

- ፕላስተር አያላጡ፡፡ በራሳቸው ግዜ ይለቃሉ፡፡
- ለቀጣይ ሰባት ቀናት መታጠብያ ገንዳ፣ ሆት ታብ ወይ ትኩስ ውሃ ላይ አይቀመጡ፡፡
- ከሂደቱ 24 ሰዓት በኋላ ገላዎን መታጠብ ይችላሉ፡፡ ባንዴጁን አይላጡት ውሃ በዝግታ እንዲፈስበት ያድርጉ፡፡
- ሂደቱ ከተካሄደ ለ48 ሰዓታት በቁስሉ ላይ ያለውን ሽፋን አይላጡ፡፡
- በዚህ አካባቢ ክሬም፣ ፓውደር፣ ሎሽን ወይ ቅባት አይጠቀሙ፡፡
- በቁስሉ አካባቢ አይሹት፣ አይከኩት ወይ ማጠብያ አይጠቀሙ፡፡
- ቁስሉ እያገገመ ካልሆነ - ቀይ፣ ለመንካት የሚያቃጥል፣ ፈሳሽ ካለው ወይ ሙቀት መጠኖ ከ100° ፋ በላይ ከሆነ በአስቸኳይ ሂደቱን ወደ ያካሄደው ሀኪም ይደውሉ፡፡

### የተለመደ ክትትል

- በተወጉበት አካበቢ አሊቭ የሚያክል እብጠት ሊሰማዎት ይችላል፡፡
- ለአንድ ሳምንት ያህል በተወጉበት አካባቢ መጠጠር፣ መበለዝና ህመም ሊሰማዎት ይችላል፡፡
- ለህመሞ አክቲሞኖፊን (እንደ Tylenol የመሳሰሉ) መውሰድ ይችላሉ፡፡ ሀይብሮፊን ወይ አስፕሪን ለመውሰድ ሀኪሞን ያናግሩ፡፡
- ለተወሰኑ ቀናት ሲነሱ ልብ ምቶ ሲቀንስ፣ ለአጭር ግዜ በፍጥነት ሊመታ ወይ ሊያዞሮት ይችላል፡፡

### ወደ 911 ይደውሉ፡

- ደረት ህመም ወይ ህመም ምልክት ካሎት፡፡ ከመውጣቶ በፊት ሀኪሞን ያናግሩ፡፡
- በተሸፈነው ወይ በቆዳ ስር ደም መድማት ካስተዋሉ፡፡ ደሙ በቆዳው ስር ከታቆረ እዚህ አካባቢ አብጦ ይጠጥራል፡፡ ይህ ከሆነ ቀጥ ብለው በመተኛት ያበጠውን አጥብቀው በመያዝ ወደ 911 ይደውሉ፡፡
- እግሮ ይቀዘቅዛል፣ ይደነዝዛል፣ ህመም ይሰማዎታል ወይ ቀለም ይቀይራል፡፡

## የታዘዘ መድሃኒት

የእንክብካቤ ቡድኖ የታዘዘሎት መድሃኒት በሚፈልጉት ፋርማሲ እንዲወስዱ ያደርጋሉ፡፡

ለእርስዎ እንዲያመቾት፣ Inova Fairfax Medical Campus ውስጥ መድሃኒት ቤት፣ Inova Pharmacy Plus፣ በምድር ቤት IHVI እንዲሁም በድንገተኛ ክፍል ውስጥ ይገኛል፡፡
ስለ Inova Pharmacy Plus የበለጠ መረጃ ለማግኘት **inova.org/pharmacyplus** ይጎብኙ፡፡

## መኪና ማሽከርከር ገደብ

ኮንሸስ ሰዴሽን ወይ አንስተዥያ ከወሰዱ በቀጣይ 24 ሰዓት ማሽከርከር አይችሉም፡፡ ቦታውን ለማግኘት ራድያል አርተሪ ጥቅም ላይ ከዋለ በቀጣይ 48 ሰዓት ውስጥ ማሽከርከር አይችሉም፡፡ ሀላፊነት ከሚሰማው አዋቂ (18 ወይ ከዛ በላይ) መሄድ ይኖርቦታል እንዲሁም የዚህን ግለሰብ ስም ለእኛ መስጠት ይኖርቦታል፡፡

## አስፈላጊ የስልክ ቁጥሮች

### Inova Fairfax Hospital

ኢንተርቨ፝ሽናልየልብትቦቅበላናማገገምያ...........................703.776.7050
*(Interventional Cardiovascular Admission and Recovery (ICAR))*

**Cath Lab ፋክስ ቁጥር** *(Cath Lab Fax)*....................**703.776.6700**

መርሀግብር ፅሀፈት ቤት *(Scheduling Office)*................**703.776.2393**

### Inova Alexandria Hospital

የልብ ትቦና ራድዮሎጂ ክፍል.......................................703.504.7950
*(Cardiovascular and Interventional Radiology Department)*

**Cath Lab ፋክስ ቁጥር** *(Cath Lab Fax)*...................**703.504.3287**

### Inova Loudoun Hospital

**Inova Heart and Vascular Institute,**
**Loudoun Campus..........................................703.858.8660**

**Cath Lab ፋክስ ቁጥር፡** *(Cath Lab Fax)*...................**703.858.8670**

## ተጨማሪ ስልክ ቁጥሮች

**ሓኪሞ፡**

---

**ፋይናንስ አገልግሎት፡**

**Inova Alexandria Hospital..............................703.504.3069**
**Inova Fairfax Hospital.....................................571.423.5750**
**Inova Loudoun Hospital .................................703.858.8091**

## Notice of Nondiscrimination

As a recipient of federal financial assistance, Inova Health System ("Inova") does not exclude, deny benefits to, or otherwise discriminate against any person on the basis of race, color, national origin, sex, disability or age in admission to, participation in, or receipt of the services or benefits under any of its programs or activities, whether carried out by Inova directly or through a contractor or any other entity with which Inova arranges to carry out its programs and activities.

This policy is in accordance with the provisions of Title VI of the Civil Rights Act of 1964, Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973, the Age Discrimination Act of 1975, Section 1557 of the Affordable Care Act, and regulations of the U.S. Department of Health and Human Services issued pursuant to these statutes at 45 C.F.R. Parts 80, 84, 91 and 92, respectively.

Inova:

- Provides free aids and services to people with disabilities to communicate effectively with us, such as:
  - Qualified sign language interpreters
  - Written information in other formats (large print, audio, accessible electronic formats and other formats)
- Provides free language services to people whose primary language is not English, such as:
  - Qualified interpreters
  - Information written in other languages

If you need these services, please let our staff know of your needs for effective communication.

If you believe that Inova has failed to provide these services or discriminated in another way on the basis of race, color, national origin, age, disability or sex, you can file a grievance by calling **703.205.2175**. You can file a grievance in person or by mail, fax or email. If you need help filing a grievance, the Patient Relations staff is available to help you.

You can also file a civil rights complaint with the U.S. Department of Health and Human Services, Office for Civil Rights, electronically through the Office for Civil Rights Complaint Portal, available at **https://ocrportal.hhs.gov/ocr/portal/lobby.jsf**, or by mail or phone at:

U.S. Department of Health and Human Services
200 Independence Ave., SW
Room 509F, HHH Building
Washington, DC 20201

**1.800.868.1019, 800.537.7697 (TDD)**

Complaint forms are available at
**http://www.hhs.gov/ocr/office/file/index.html**

# Interpreter Services are available at no cost to you.

## Please let our staff know of your needs for effective communication.

| | |
|---|---|
| **Spanish** | Atención: Si usted habla español, tiene a su disposición servicios gratuitos de asistencia con el idioma. Por favor infórmele a nuestro personal sobre sus necesidades para lograr una comunicación efectiva. |
| **Korean** | 알려드립니다: 귀하가 한국어를 구사한다면 무료 언어 도움 서비스가 가능합니다. 효과적인 의사전달을 위해 필요한 것이 있다면 저희 실무자에게 알려주시기 바랍니다. |
| **Vietnamese** | Chú ý: Nếu quý vị nói tiếng Việt, dịch vụ hỗ trợ ngôn ngữ có sẵn miễn phí cho quý vị sử dụng. Xin vui lòng thông báo cho nhân viên biết nhu cầu của quý vị để giao tiếp hiệu quả hơn. |
| **Chinese** | 注意：如果你說中文，可以向你提供免費語言協助服務。請讓我們的員工了解你的需求以進行有 效溝通。 |
| **Arabic** | انتباه: إذا كنت تتحدث العربية، تتوافر الخدمات المجانية للمساعدة في اللغة. يرجى إعلام فريق العمل باحتياجاتك من أجل الحصول على عملية تواصل فعالة. |
| **Tagalog** | Atensyon: Kung nagsasalita ka ng Tagalog, mayroong magagamit na mga libreng serbisyong tulong sa wika para sa iyo. Mangyaring ipaalam sa aming mga kawani ang iyong mga pangangailangan para sa epektibong komunikasyon. |
| **Farsi** | توجه: اگر به زبان فارسی صحبت می کنید، تسهیلات زبانی به صورت را یگان برای شما فراهم خواهد بود. به منظور برقراری ارتباط موثر، کارکنان ما را از نیازهای خود مطلع کنید. |
| **Amharic** | ትኩረት፡ አማርኛ የሚናገሩ ከሆነ ለእርስዎ የቋንቋ ድጋፍ አግልግሎቶች ከክፍያ በነጻ ይቀርብልዎታል፡፡ ውጤታማ የሆነ ኮሚዩኒኬሽን የሚፈልጉ ከሆነ ሰራተኞችን እንዲያውቅ ያድርጉ፡፡ |
| **Urdu** | توجہ: اگر آپ اردو بولتے ہیں تو، زبان امداد خدمات، مفت میں، آپ کو دستیاب ہیں۔ موثر مواصلت کے لیے برائے مہربانی ہمارے عملہ کو اپنی ضروریات کے بارے میں بتلا دیں۔ |
| **French** | Attention: Si vous parlez Francais, des services d'aide linguistique vous sont proposés gratuitement. Veuillez informer notre personnel de vos besoins pour assurer une communication efficace. |
| **Russian** | Внимание: Если вы говорите на русском языке, для вас доступны бесплатные услуги помощи с языком. Для эффективной коммуникации, пожалуйста, дайте персоналу знать о ваших потребностях. |
| **Hindi** | कृपया ध्यान दें : यदि आप हिन्दी बोलते है, तो आपके लिए निःशुल्क भाषा सहायता सेवा उपलब्ध है। कृपया प्रभावी संचार-संपर्क हेतु अपनी आवश्यकताओं के बारे में हमारे कर्मचारियों को बताएं। |
| **German** | Achtung: Wenn Sie Deutsch sprechen, stehen kostenlose Service-Sprachdienstleistungen zu Ihrer Verfügung. Teilen Sie unserem Team bitte Ihre Wünsche für eine effektive Kommunikation mit. |
| **Bengali** | দৃষ্টি আকর্ষণ করুন : আপনি যদি বাংলা বলতে পারেন, তাহলে আপনার জন্য বিনামূল্যে ভাষা সহায়তা সেবা পাওয়া যাবে। অনুগ্রহ করে কার্যকরী যোগাযোগের জন্য আপনার প্রয়োজনীয়তার বিষয়ে আমাদের কর্মীদের জানান। |
| **Kru (Bassa)** | Tò Ɖùǔ Nɔ̀mɔ̀ Dyíin Cáo: Ɔ jǔ ké m̀ dyi Gɔ̀ɖɔ̃ɔ̀-wùɖù (Ɓǎsɔ́ɔ̀-wùɖù) po ní, nìí, à ɓéɖé gbo-kpá-kpá ɓó wuɖu-dù kò-kò po-nyɔ̀ ɓě bìì nɔ̃ à gbo ɓó pídyi. M̀ dyi ɖɛ ɖò mɔ́ nɔ̃ à gbo ní, m̀ mɛ nyuɛ ɓɛ́ à kůà-nyɔ̀ ɓěɔ̀ kéɛ dyí dyuò, ké à kè mɔ̀ kè muɛ jè cɛ̃ìn nɔ̀mɔ̀ dyíin. |
| **Ibo** | Nrụbama: Ọ bụrụ na ị na asụ Igbo, ọrụ enyemaka asụsụ, n'efu, dịịrị gị. Biko mee ka ndị ọrụ anyị mara mkpa gị maka nkwukọrịta ga-aga nke ọma. |
| **Yoruba** | Akiyesi: Bi o ba nsọ Yoruba, awọn iṣẹ iranilọwọ ede wa l'ọfẹ fun ọ. Jọwọ jẹ ki ara ibiṣẹ wa mọ nipa awọn aini rẹ fun ibaraẹnisọrọ ti o munadoko. |

INOVA®

**Inova Alexandria Hospital**
**Inova Heart and Vascular Institute**
**4320 Seminary Rd.**
**Alexandria, VA 22304**
**703.504.3000**

### መኪና መቆምያ

በኖርዝ ሀዋርድ መንገድ አቅራብያ መኪና ማቆምያ ይገኛል:: ነፀ ቫለት መኪና መቆምያ በታካሚወች መግብያ አካባቢ ከሰኞ እስከ ዓርብ 5:30 ጥዋት – 7:30 ከሰዓት ይገኛል::

### መጓዣ አቅጣጫ

*ከ አርሊንገተን ወይ ዋሽንግተን ዲሲ:* ከሳውዝ I-395 ወደ ሰሚኒሪ መንገድ ይውጡ:: ወደ ኢስት በግራ ይሂዱ:: አራት ብሎክ ይሂዱ:: ሆስፒታሉ በቀኝ በኩል ከሰሚናሪ መንገድና ኖርዝ ሀሃዋርድ መንገድ ላይ ይገኛል::

*ከሪችመንድ:* ወደ ስፕሪንፊልድ I-95 ኖርዝ ይጠቀሙ:: ሁለት ምርጫ ይኖሮታል I-495, I-395 እንዲሁም I-95:: ወደ 395 ኖርዝ ሰሚናሪ መንገድ ይቀጥሉ:: ወደ ኢስት በቀኝ ይታጠፉ:: አራት ብሎክ ይሂዱ:: ሆስፒታሉ በቀኝ በኩል ከሰሚናሪ መንገድና ኖርዝ ሀሃዋርድ መንገድ ላይ ይገኛል::

**Inova Fairfax Medical Campus**
**Inova Heart and Vascular Institute**
**3300 Gallows Rd.**
**Falls Church, VA 22042**
**703.776.4001**

### የታካሚዎች መግብያና መኪና ማቆምያ

ወደ Inova Fairfax Medical Campus ከዉድበርን መንገድ ወደ ዌልነስ ቡልቫርድ ይግቡ:: Inova Fairfax Hospital Surgery Center እንዲሁም Inova Heart and Vascular Institute በማለፍ ወደ ግረይ ጋራዥ በቀኝ በመታጠፍ ያቁሙ:: ወደ ደረጃ G ሊፍት ይጠሙ:: ወደ ህንፃው በምድር ቤት በመግባት ወደ ልብ ህክምና Cath Lab/EP Lab እንግዳ መቀበያ ይግቡ::

### መጓዣ አቅጣጫ

#### በ I-495 (ካፒታል ቤልትወይ)

*ከኖርዝ (ታይሰን):* 51 ይጠቀሙ:: በራምፑ ላይ ግላውስ መንገድ ወደ ውድበርን መንገድ ይሻገሩ:: በመጀመርያው መብራት ወደ ቀኝ ዌልነስ ብሉቫርድ ይታጠፉ:: Inova Fairfax Hospital Surgery Center እንዲሁም Inova Heart and Vascular Institute በማለፍ በቀኝ በኩል ወደ ግረይ ጋራዥ ይግቡ::

*ከሳውዝ (አሌክሳንድርያ/ስፕሪንግፊልድ):* 51 ይጠቀሙ:: በራምፑ በላይ ከሚገኘው የትራፊክ መብራት ወደ ግላውስ መንገድ በግራ ይታጠፉ:: ወደ ዉድበርን መንገድ በግራ ይታጠፉ:: ወደ መጀመርያው የትራፊክ መብራት በመሄድ ወደ ዌልነስ ቡልቫርድ በቀኝ ይታጠፉ:: Inova Fairfax Hospital Surgery Center እንዲሁም Inova Heart and Vascular Institute በማለፍ በቀኝ በኩል ወደ ግረይ ጋራዥ ይግቡ::

#### በ መንገድ 50

*ከዌስት (Fairfax):* የሚወጡት ወደ 650/ ጋሎውስ መንገድ:: በላይኛው ራምፕ፣ ወደ ግሎውስ መንገድ:: ወደ ጋሎው መንገድ በመሄድ ወደ በቀኝ በኩል ዊድበርን መንገድ ይታጠፉ:: ወደ መጀመርያው የትራፊክ መብራት በመሄድ ወደ ዌልነስ ቡልቫርድ በቀኝ ይታጠፉ:: Inova Fairfax Hospital Surgery Center እንዲሁም Inova Heart and Vascular Institute በማለፍ በቀኝ በኩል ወደ ግረይ ጋራዥ ይግቡ::

*ከኢስት (ዋሽንግተን/ፋልስ ቤተ ክርስትያን):* በ I-495 በማለፍ ወደ 650/ጋላውስ መንገድ ይውጡ:: በራምፑ በሚገኘው መብራት፣ በግራ ወደ ጋላውስ መንገድ መታጠፍ:: ወደ ጋሎው መንገድ በመሄድ ወደ በቀኝ በኩል ዊድበርን መንገድ ይታጠፉ:: ወደ መጀመርያው የትራፊክ መብራት በመሄድ ወደ ዌልነስ ቡልቫርድ በቀኝ ይታጠፉ:: Inova Fairfax Hospital Surgery Center እንዲሁም Inova Heart and Vascular Institute በማለፍ በቀኝ በኩል ወደ ግረይ ጋራዥ ይግቡ::

**Inova Loudoun Hospital**
**Schaufeld Family Heart Center**
**44035 Riverside Pkwy., Suite 120**
**Leesburg, VA 20176**
**703.858.8660**

### መኪና መቆምያ

ከህኪም ፅህፈት ቤት II (ህንፃ 44035) ፊት ለፊት ነፃ ቫሌት ፓርኪንግ ይገኛል::

### መጓዣ አቅጣጫ

*ከለስበርግና ፖይንት ዌስት:* መስመር 7 ኢስት ይጠቀሙ:: ወደ ላድስዎን ቦሊቫርድ ይውጡ:: በመጀመርያ በሚያገኙት ቁም በሚል ምልክት በቀኝ ወደ ሪቨርሳይድ ፓርክወይ ይታጠፉ:: ወደ ሆስፒታሉ ዋና መግብያ የመጀመርያውን ቀኝ ይጠቀሙ::

*ከታይሰን ኮርነርና ፖይንት ኢስት:* መስመር 7 ዌስት ይጠቀሙ:: ወደ ላድስዎን ቦሊቫርድ ይውጡ:: በመጀመርያ በሚያገኙት ቁም በሚል ምልክት በቀኝ ወደ ሪቨርሳይድ ፓርክወይ ይታጠፉ:: ወደ ሆስፒታሉ ዋና መግብያ የመጀመርያውን ቀኝ ይጠቀሙ::

*ከዱላስ ሳውዝና ፖይነት ሳውዝ:* ሎውደን ካውንቲ ፓርክወይ ይጠቀሙ:: በግራ ወደ ኤቨርግሪን ማይስ መንገድ ይታጠፉ:: በቀኝ ወደ ቤልሞንት ሪጅ መንገድ ይታጠፉ:: በቀኝ ወደ መስመር 7 ኢስት ይታጠፉ:: ወደ ላድስዎን ቦሊቫርድ ይውጡ:: በመጀመርያ በሚያገኙት ቁም በሚል ምልክት በቀኝ ወደ ሪቨርሳይድ ፓርክወይ ይታጠፉ:: ወደ ሆስፒታሉ ዋና መግብያ የመጀመርያውን ቀኝ ይጠቀሙ::

G37634AM/12-19/pdf

INOVA®